የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሣኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.17
ADDIS ABABA 20st February, 2024


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፩/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመው ስምምነት ማፀደቂያ አዋጅ ......................................ገጽ ፲፭ሺ፫፻፲፫


## Content


Proclamation No. 1311/2023

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Lebanon on the Employment of Ethiopian Workers in Lebanon Ratification Proclamation ………… .....Page 15,313


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፩/፪ሺ፲፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመውን ስምምነት ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የቆየውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር በማስፈለጉ፤

በሊባኖስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው እና መብትና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ በአገራቱ ፍላጎት ያለ በመሆኑ፣

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እ.ኤ.አ. ኤፕሪል ፲፩ ቀን ፪ሺ፳፫ የፈረመው በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ባካሄደው ፰ኛ መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1311/2023

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF LEBANON ON THE EMPLOYMENT OF ETHIOPIAN WORKERS IN LEBANON

**WHEREAS,** to further strengthen existing bilateral relation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Lebanon;

**WHEREAS**, a desire exists for Ethiopian workers in Lebanon to have a legal framework and to protect their rights;

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has signed the said Agreement on 11th day of April, 2023;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 8th Regular session held on 14th day of December, 2023;

**NOW, THERERORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመው ስምምነት ማፀደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፩/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሊባኖስ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈፃሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በኢትዮጵያና በሊባኖስ መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመውን ስምምነት የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Lebanon on the Employment of Ethiopian Workers in Lebanon Ratification Proclamation No. 1311 /2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Lebanon on the Employment of Ethiopian Workers in Lebanon is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Labor and Skills of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Lebanon on the Employment of Ethiopian Workers in Lebanon.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa on this 20th day of February, 2024.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**